# <u>የአዲስ አበባ ልማት ዘላቂና ፍትሃዊ እንዲሆን ለማስቻል…</u>

*<u>ፀሃፊ፡ ሰዊት ሰለሞን</u>* (e-mail: tigsolmich@gmail.com)

***መግቢያ***

*አዲስ አበባ በፈጣን ዕድገት ላይ ከሚገኙ የዓለማችን ከተሞች ከቀዳሚዎቹ መሃል ትጠቀሳለች፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ እየታዩ ያሉት የልማት እንቅስቃሴዎች እጅግ በጣም ተስፋ ሰጭዎችና ከተማዋን ካደጉ የዓለም ከተሞች ተርታ ሊያሰልፉዋት የሚችል አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ የተከናወኑትና እየተከናወኑ ያሉት የመንገድ፣ የቀላል ባቡር መስመር፣ የመኖሪያ ቤት፣ የተለያየ አገልግሎት እንዲሰጡ የታሰቡ ህንፃዎች ግንባታዎች እና የተለያየ ደረጃ ያላቸው ኢንዱስትሪዎች ግንባታዎች ሲታዩ በእርግጥም አዲስ አበባ በፈጣን የዕድገት ጎዳና ላይ ያለችና ከመሰረቱ እየተለወጠች መሆንዋን የሚያሳዩ ምስክሮች ናቸው፡፡ የከተማዋ ዕድገት በሀገሪቱ ውስጥ ያለው አጠቃላይ ዕድገት አንድ አካል ሆኖ ሊታይ የሚችል እና በሌላ መልኩ ሀገሪቱ በከፍተኛ የልማት ዕድገት ላይ ለመሆንዋ ሁነኛ ማሳያ ነው፡፡*

*ከተማዋ በከፍተኛ ዕድገት ላይ ስለመሆንዋ ብዙ የተባለለት ነው፡፡ በተለይ በተለያየ አጋጣሚ ወደ ከተማዋ የመጡ የውጭ ዜጎች በከተማ ፈጣን ለውጥ እጅግ እየተደነቁ መሆኑን በተለያዩ ድረገፆችና የውጭ መገናኛ ብዙሃን ላይ በሚያቀርቧቸው ፅሁፎች በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ ከመደነቃቸው የተነሳም "ከተማዋ በሙሉ አንድ የኮንስትራክሽን ሳይት ትመስላለች" ሲሉ ይደመጣሉ፡፡*

*አዲስ አበባ የሃገሪቱ ዋና ከተማ ከመሆንዋ ባለፈ የሃጉራዊና ዓለምአቀፋዊ ተsማት መቀመጫ እንደመሆንዋ እና ከዚህም ጋር ተያይዞ በዛ ያሉ የዲፕሎማቲክ አባላት መቀመጫ ስለሆነች መንግስትም ሆነ የከተማዋ አስተዳደር አዲስ አበባን ተወዳዳሪና ተመራጭ እንድትሆን ለማስቻል ዓለምአቀፋዊ ደረጃን የጠበቀች ከተማ የማድረግ ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታ አለባቸው፡፡ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በከተማዋ ውስጥ የሚደረጉ የልማት ሥራዎች ደግሞ መንግሥት ይህን ኃላፊነቱን በመረዳት ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እያደረገ ስለመሆኑ ማሳያ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡*

*የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ ይህ ፈጣን ዕድገትና የልማት እንቅስቃሴ ዘላቂነቱ ተረጋግጦ በውጤቱም ሕዝቡ ተጠቃሚና ደስተኛ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የውይይት መነሻ ሃሳብ በማቅረብ ባለሙያዎችና የሚመለከታቸው አካላት ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡ ማድረግና በሂደቱም የከተማዋ አስተዳደር ለፖሊሲ ማመንጨት የሚረዱት ገንቢ ሃሳቦችን እንዲያገኝ ማገዝ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ልማት ዘላቂ ኢንዲሆን ለማድረግ የመስኩ ባለሙያዎችና የሙያ ማህበራት (የከተማ ፕላን ባለሙያዎች ማህበር፣ የአርክቴክቶች ማህበር፣ የኤኮኖሚስቶች ማህበር፣ የሲቪል ምህንድስና ባለሙያዎች ማህበር፣ የሶሺዩሎጂስቶች ማህበር ወዘተ…) ለፖሊሲ አውጪው አካል ሃሳብ*

የማቅረብ ውዴታ ብቻ ሳይሆን ሙያዊ ግዴታም አለባቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህንንም ያልኩት ጉድለቶች እንዳይፈጠሩ መጀመሪያውኑ ከመርዳት ይልቅ ከተከሰቱ በኃላ ዳር ሆኖ መተቸት ማንንም የሚረዳ አይደለምና ነው፡፡ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢም ዋና ዓላማ ይኸው ነው፡፡

ስለ ዘላቂ ልማት ሲታሰብ መሠረታዊው ጉዳይ በምንፈልገው ልማትና በተፈጥሮአዊው አካባቢያችን መሃከል ሊኖር ስለሚገባው ዘላቂነት ያለው መስተጋብር ማሰብ ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አንድ ልማት ዘላቂና ጤናማ ነው የሚባለው በምንም ዓይነት መልኩ በአካባቢያችን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያሳድርና በአሁኑም ሆነ በመጪው ትውልድ ላይ ችግር የማያስከትል መሆኑ ሲረጋገጥና ሁሉም የከተማ ነዋሪ በእኩልነት የተስተናገደበት ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ሲባል ነው በዓለማችን ስለአረንጓዴ ልማት እንዲሁም ሁሉን ተጠቃሚ ሰለሚያደርግ ልማት ትኩረት መሰጠት እንዳለበት መነገር የጀመረው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ አገራችንም የአረንጓዴ ልማት ፖሊሲ በመቅረፅና የሁሉንም ዜጋ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ልማት ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እያደረገች ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማም ሰፊ የልማት እንቅስቃሴ እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን ልማቱ ዘላቂ እንዲሆን ደግሞ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህ ሲባል ግን እስካሁን በመካሄድ ላይ ባለው የልማት እንቅስቃሴ ዘለቄታዊነትን እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ምንም ጥረት አልተደረገም ለማለት ሳይሆን በአንዳንድ አካባቢ በሚካሄዱ የልማት ሥራዎች ምክንት የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመቀነስ ወይም ለማስቀረት ተገቢው ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ለማለት ነው፡፡ ከዚህ መሰረታዊ ሃሳብ በመነሳት ሁለንተናዊ የከተማዋ የልማት እንቅስቃሴዎች ውጤታቸው ለነዋሪዎችዋና ለጎብኝዎችዋ ለኑሮ፣ ለሥራና ለመዝናናት አመቺ፣ ተወዳዳሪ እና ተመራጭ የሆነች ከተማ እንድትሆን ማድረግ እንዲያስችሉ የሚከተሉት ጉዳዮች የልማት እንቅስቃሴውን ዘላቂነት ከማረጋገጥ ረገድ ካላቸው ከፍተኛ ሚና አንፃር ተለይተው ለውይይት መነሻነት ቀርበዋል፡፡

## 1. አረንጓዴ ልማትን ማረጋገጥ

ሁሉም አይነት የልማት እንቅስቃሴ አነሰም በዛ በተፈጥሮ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ አሉታዊ ተፅዕኖዎቹ ለዘላቂ ልማት መረጋገጥ በጎ ድርሻ ያላቸው መሆኑ የሚያግባባ ስለሆነ የፅሁፉ ሙሉ ትኩረት አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖራቸው በሚችሉ ጉዳዮች በዋናዎቹ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

ስለዘለቄታዊ ልማት ሲወራ ስለአረንጓዴ ልማት ማውራት መሆኑን ሁሉም እንደሚረዳው ታሳቢ በማድረግ፣ እየታየ ያለው የአዲስ አበባ ልማት ዘለቄታዊ እንዲሆን ለማድረግ ከተፈለገ ልማቱ

በተፈጥሮ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሌለው እንዲሆን መጣር፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ተፅዕኖው ዘለቄታዊነትን የመፈታተን ደረጃ ላይ የደረሰ እንዳይሆን ማረጋገጥ ተገቢና የግድም ይሆናል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ሁኔታ ስለአረንጓዴ ልማት ስናወራ ከሚደረገው መጠነ ሰፊ የልማት ዕንቅስቃሴ ጎን ለጎን ከዚህ በታች በተዘረዘሩትና የአካባቢን ህልውና ሊያረጋግጡ በሚችሉ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባዋል፡፡

## a. ነባር አረንጓዴ ቦታዎችን ማስከበር፣ ማደራጀትና መንከባከብ

በአዲሰ አበባ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ዕጥረት የሚታይባቸውና ተገቢውም ትኩረት ያልተሰጣቸው የነባር አረንጓዴ ቦታዎች እንክብካቤ ጉዳይ ነው፡፡ ነባር አረንጓዴ እና በየሰፈሩ የሚገኙ ክፍት መጫወቻ ቦታዎች በልማት ስም ኮንስትራክሽን አርፎባቸዋል የተረፉትም ቢሆኑ ተገቢው ጥበቃና እንክብካቤ ስለማይደረግላቸው ካለመኖር የመቆጠር ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡

ለዚህ ማሳያ ብዙ ቦታዎችን መጥቀስ ቢቻልም በተለይ የአዲስ አበባ ከተማ ልዩ መለያ የሆነው ከከተማዋ ሰሜን አቅጣጫ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ተዘርግቶና ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ ለከተማዋ ግርማ ሞገስ የሆነውና በአብዛኛው በባህር ዛፍ የተሸፈነው ደን ይዞታ አዳዲስ በሚሰሩ ግንባታዎች እየተመናመነ ይገኛል፡፡ ይህ እንደ ከተማዋ መተንፈሻ ሳንባ ሊቆጠር የሚገባው ደን ከተማዋ ጤናማና ምቹ የአየር ሁኔታ እንዲኖራት መሪውን ሚና እየተጫወተ የሚገኝ እንደመሆኑ ከፍተና የሆነ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግለት የሚገባ ነው፡፡ የዚህ ደን መጥፋት የከተማዋን አየር ሁኔታ ምን ያህል ሊያዛባ እንደሚችል መገመት ከባድ አይሆንም፡፡ ይህ ደን ከከተማዋ መስፋት ጋር ተያይዞ እየተወረረ የሚገኝ ሲሆን በተለይ ባለሃብቶች ባለፎቅ መኖሪያ ቤቶችን ውድድር በሚመስል መልክ እየገነቡበት ይገኛል፡፡ ስለሆነም የከተማውም ሆነ የወረዳ አስተዳደሮች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተውት ጥበቃና እንክብካቤ ሊያደርጉለትና ይልቁንም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያመጣ በሚችል መልኩ መጠቀም የሚቻልበትን መንገድ ሊያመቻቹ ይገባል፡፡

ከዚህ ውጭ በመንደር፣ በወረዳ፣ በክፍለከተማ እና በከተማ ደረጃ ከመወረር ተርፈው የሚገኙ ክፍት መጫወቻና መናፈሻ ቦታዎችን ህጋዊ በማድረግ፣ በማጠር እና በመንከባከብ የከተማዋ መተንፈሻ ሆነው እንዲቀጥሉ ማስቻል ለነገ ሊባል የማይገባው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የከተማዋም ፕላን እነዚህ ክፍት ቦታዎች እንዲጠበቁ የራሱን ሚና መጫወት ይገባዋል፡፡

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እነዚህን መጠነ ሰፊ ጥቅም ያላቸውን ቦታዎች በልማት ስም ካጣናቸው በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት አሉታዊ ተፅዕኖ ከባድ ዋጋ የሚያስከፍሉ እና ዕዳውም ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡

ስለሆነም በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት አስተዳደር እርከኖች ከሕዝቡና ከልማት አጋሮች ጋር በመሆን ነባር አረንጓዴ እና ሌሎች ክፍት ቦታዎችን ማስከበር፣ መጠበቅ፣ ማደራጀትና መንከባከብ ይገባቸዋል፡፡ ለዚህም ሲባል ለሌላው የመሰረተ ልማት አገልግሎት እንደተሰጠው ትኩረት ሁሉ ለዚህም ሥራ ተገቢው ባለቤት ተለይቶለት በጀት ሊመደብለት ይገባል፡፡

## b. አዳዲስ አረንጓዴ ቦታዎችን መፍጠር

ነባር አረንጓዴ ቦታዎችን ከመጠበቅ በተጨማሪ ከተማዋ ከሚያስፈልጋት አረንጓዴ ቦታዎች መጠን አንፃር ገና ብዙ የሚቀራት በመሆኑ አዳዲስ አረንጓዴ ቦታዎችን እየተካሄዱ ካሉ የልማት ሥራዎች ጋር አያይዞ ማስፋፋት የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ ከመንደር ደረጃ አንስቶ እስከ ከተማ አቀፍ ደረጃ የሚደርሱ አረንጓዴ ቦታዎችን በየደረጃው መፍጠር፣ ማደራጀት እና መንከባከብ ይገባል፡፡ በኮንደሚኒየም ቤቶች ግንባታ፣ በሪል እስቴት ቤቶች ግንባታ እና በሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር ደረጃውን የጠበቁና በቂ ስፋት ያላቸው አረንጓዴ ቦታዎች ተካተው ሊሰሩ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ አንዳንድ ጥረቶች ቢታዩም በቂ ነው ተብሎ አይታመንም፡፡ በተለይ በሪል እስቴት አልሚዎች በኩል የግንባታ ፍቃድ ሲወስዱ በሳይት ፕላናቸው ላይ የሚታዩት አረንጓዴ ቦታዎችና ፓርኪንግ ቦታዎች ወደ ተግባር ሲገቡ በሙሉ ጠፍተው ማየት የተለመደ ሲሆን ይህም የግንባታ ፍቃድ ከተሰጠ በኃላ በሚመለከተው መሥሪያ ቤት ቁጥጥር የሌለ መሆኑን ያሳያል፡፡

ከተማዋ በአሁኑ ጊዜ ይህ ነው የሚባልና ሕዝቡ በምቾት ሊዝናና የሚችልበት፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ሊያጫውቱ የሚችሉበት፣ በእግር ለመንገዝ ወይም ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችሉ፣ የሙዚቃና ሌሎች መዝናኛ ዝግጅቶችና ኮንሰርቶች ሊደረጉ የሚችሉበት እንዲሁም ለሌሎች መሰል አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ክፍት ቦታዎች በየአካባቢው የሉም በሚያስብል ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡፡

ስለሆነም የከተማው አስተዳደር ችግሩን ለመቅረፍ ከፍተኛ ሥራ ይጠብቀዋል፡፡ ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉ ቦታዎች በከተማው ፕላን እንዲለዩ ከማድረግ ጀምሮ እንዲከለሉና በተቀናጀ መልክ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ ማድረግ ከተማዋ ጤናማና ተወዳጅ

እንድትሆን ከማድረግ በተጨማሪ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ያለው አዎንታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን እየተለፋበት ያለው ሰፊና ዘርፈ ብዙ የከተማ ልማት እንቅስቃሴ የሚፈለገውን ያህል ውጤት አይኖረውም፤ ዘለቄታዊነቱም ያልተረጋገጠ ይሆናል፡፡ የከተማዋም ምቹነት፣ ተወዳዳሪነትና ተመራጭነት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል፤ ከተማዋም አሰልቺ እንድትሆን ያደርጋል፡፡

## c. ወንዞችን ከብክለት መከላከል እና ማልማት

አዲስ አበባ በወጣገባ ቦታ ላይ የተመሰረተችና በተራሮች የተከበበች በመሆንዋ ትንሽ የማይባሉ ወንዞች በውስጥዋ ይገኛሉ፡፡ ድሮ ድሮ እነዚህ ወንዞች በልዩ ልዩ ተክሎች የተከበቡ፣ ዋና ለመዋኘት (ብዙዎች የከተማዋ ልጆች ዋና የለመዱት በነዚህ ወንዞች ውስጥ ነው)፣ ለአነስተኛ መስኖ ወይም ከተማ ግብርና ሥራ፣ ገላ ለመታጠብ፣ ልብስ ለማጠብና ለመሳሰሉት ሌሎች አገልግሎቶች ይውሉ እንደነበር ይታወቃል፡፡ አሁን አሁን ምን ያህሉ ወንዞች ከላይ ለተጠቀሱት አገልግሎቶች እንደሚውሉ መገመት ለማናችንም የሚከብድ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ የአብዛኛው ሰው መልስ "ሁሉም ወንዞች በመበከላቸው ምክንያት ውሃቸውን መጠቀም ቀርቶ በመጥፎ ሽታቸው ምክንያት አጠገባቸው እንኳን መድረስ አይቻልም" ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡

የአዲስ አበባ ወንዞች በግድየለሽነት ለደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃነት ውለዋል፤ ኢንዱስትሪዎች በኬሚካል የተበከለ መርዛማ ፍሳሾችን ወደ ወንዞች ይለቃሉ፤ ለወንዞቹ እንደጥብቅ (buffer area) ሊያዝ በሚገባው ቦታ የተለያዩ ግንባታዎች ተሰርቶበት የወንዞቹ ተፈጥሯዊ ፍሰት መስመሩ ወይም መውረጃው ተጣቧል፤ ባጠቃላይ አሁን ያለው ሁኔታ ሲታይ ለከተማዋ ወንዞች ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱ ምክንያት ለከፍተኛ ብክለት የተዳረጉ በመሆኑ ምክንያት በሰዎች፣ በአትክልቶችና በእንስሳት ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡ ከጉዳዩ አስጊነትና በአካባቢ ላይ ከሚያሳድረው አስከፊ ጉዳት አንፃር የከተማዋን ወንዞች የመታደግ ጉዳይ ለነገ ሊባል የሚገባው ጉዳይ አይደለም፡፡ ሁኔታው ልክ ቀይ መብራት የበራበትና የነፍስ አድን ያክል አስቸኳይ መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

አዲስ አበባ ወንዞችዋን መታደግ ይገባታል፤ ይህ ሁሉንም የሚያስማማ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህም ተገቢውን የሕግ ማዕቀፍ ከማዘጋጀት ጀምሮ በከተማው ፕላን የተደገፈና በሙያ የታገዘ የወንዞች ጥበቃና ልማት ሥራ መከናውን ይገባዋል፡፡ የከተማዋ ወንዞች የአካባቢ ብክለት

ምንጭ መሆናቸው ቀርቶ የመዝናኛና የውበት ተምሳሌት እንዲሆኑና ከዚያም አልፈው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲኖራቸው መደረግ ይገባቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በተጓዳኝ የከተማውን ነዋሪ ባህሪይ በመለወጥ ወንዞችን በማዳን ሥራው ላይ እንዲሳተፍ ብዙ ሥራ ሊሰራ ይገባዋል፡፡

## d. የዛፍ ተከላ በመደበኛነት ማካሄድ

እንደዚህ ፅሁፍ አቀራቢ ዕምነት አዲስ አበባ ለብክለት በጣም የተጋለጠች ከተማ ነች፡፡ ለዚህም እንደምክንያት ከሚጠቀሱት መሃል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አካባቢ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ችግሮች በሙሉ የፈጠሩት የአካባቢ ብክለት ሥጋት፤
- በከተማዋ ውስጥ ያሉት መኪኖች ቁጥር ከተመሳሳይ የሌሎች ሃገሮች ከተሞች አንፃር ሲታይ አነስተኛ ቢሆንም ከአሮጌነታቸው አንፃር ሲታይ ግን የሚፈጥሩት የአካባቢ ብክለት ሥጋት ከፍተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን መታየት የጀመረ ክስተት መሆኑ፤
- በከተማዋ ውስጥ በሰፊው የሚካሄዱት የልማት እንቅስቃሴዎች ለአካባቢ ጥበቃ የሚሰጡት ትኩረት አናሳ መሆኑና ይህም ተፅዕኖ ማሳደር መጀመሩ፤
- የከተማዋ የቆሻሻ አወጋገድና ሳኒቴሽን ሁኔታዎች ገና ብዙ ሥራ የሚፈልጉ መሆኑና ያልዘመኑ መሆኑ በአካባቢ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ የከፋ መሆንና ይህም በከተማዋ ውስጥ በጉልህ እየተስተዋለ መሆኑ፤
- አብዛኛው የከተማው ነዋሪ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆኑና የኢነርጂ አጠቃቀሙ ኃላቀር የኑሮ ዘይቤ የሚከተል በመሆኑ እንዲሁም እያንዳንዱ ነዋሪ ለአካባቢ ጥበቃ ሚና እንዳለው ባለመረዳቱ ምክንያት አካባቢን በመበከል ረገድ አስተዋፅዖ እያደረገ መገኘቱ፤
- ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ ኃላፊነት የተሰጣቸው የፌዴራል ሆነ የከተማ አሰተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች በአብዛኛው ህግ ከማውጣት ባለፈ እርምጃ የመውሰድ ሆነ የማስወሰድ ፍላጎታቸውና አቅማቸው ሲታይ ውሱንና ዕምነት የሚጣልበት ባለመሆኑ፤

ባጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም መሰል ችግሮች ከተማዋ ለአካባቢ ብክለት በእጅጉ የተጋለጠች መሆንዋ እና አንዳዶቹም ብክለትን ካሁኑ እያስከተሉ መሆኑን መቀበል የግድ ይላል፡፡

ይህንን ብክለት ለመከላከል መከናወን የሚገባቸው ሥራዎች እንዳሉ ሆኖ ያለውን ብክለት ለመቀነስ እንዲቻል ዛፎችን መትከል ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይታወቃል፡፡ ዛፎች

የአካባቢ አየርን ከማጥራትና ነፋሻ አየር ከመስጠት በተጨማሪ ለከተማው ውበት ይሰጣሉ፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሃገሪቱ እየተደረገ ያለው የደን ልማትና የዛፍ ተከላ በመጠኑም ቢሆን በአዲስ አበባ ውስጥም እየተደረገ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የዛፍ ተከላ ሥራው ከዘመቻ ሥራነት ተላቆ በመደበኛነትና በባለሙያ በተደገፈ ሁኔታ መከናወን ይገባዋል፡፡ ይህም ሥራ ከቤተሰብ ደረጃ ተነሥቶ በወረዳ፣ በክፍለ ከተማ እና በከተማ ደረጃ በተቀናጀ መልኩ በሥርዓት መከናወን ይገባዋል፡፡ የዛፍ ተከላ ሥራው በመኖሪያ ግቢዎች፣ በመንገድ አካፋይና ዳርቻዎች፣ በመናፈሻዎችና ሌሎች ክፍት ቦታዎች፣ በወንዝ ዳርቻዎች፣ ለደን በተከለሉ ቦታዎችና በተዳፋታማ አካባቢዎች ላይ ሁሉ መካሄድና ከተተከለም በኃላ ተገቢው እንክብካቤ ማድረግ የግድ ይላል፡፡ ይህ ሁሉ ሲደረግ ደግሞ ህብረተሰቡንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ከዕቅድ ማውጣት እስከ ማስፈፀም ደረጃ ድረስ በማሳተፍ የባለቤትነት ስሜት በመፍጠር በመንከባከቡ ረገድ ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 2. **የገቢ ልዩነት ያላቸው መንደሮች እንዳይፈጠሩ ማድረግ** (prevent segregation)

ቀደም ባሉት ጊዜያት አዲስ አበባ ከምትታወቅባቸው ባህሪዎች መሃል አንዱ በሁሉም አካባቢ ደሃና ሃብታም አብሮ መኖሩና በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዬች ተባብሮና ተጋግዞ መኖሩ ነው፡፡ ይህም ከተማዋን ከአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ከተሞች በተለየ ሁኔታ የወንጀል መጠኑ የቀነሰባት ከተማ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ይህንንም መልካም ገፅታ በተለያየ ምክንያት ወደ ሃገሪቱ የሚመጡ የውጭ ሃገር ዜጎች በአድናቆት ሲናገሩት ማድመጥ የተለመደ ነው፡፡ ይህ የአብሮ መኖር ልምድ ታዲያ ማንኛውም ዋጋ ተከፍሎም ቢሆን ሊጠበቅ የሚገባው መልካምና የሚወደስ እሴት ነው፡፡

ነገር ግን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተፈጠሩ ያሉ ሰፈሮች ይህን መልካም እሴት የሚንዱ አይነት ናቸው፡፡ እነዚህ አዳዲስ ሰፈሮች ሙሉ በሙሉ በሚያስችል ሁኔታ ከፍተኛ ወይም መሃከለኛ ገቢ ያላቸውና ከተለመደው የአዲስ አበባ አብሮና ተጋግዞ የመኖር ዘይቤ በተቃራኒ ግላዊና ጎረቤት ከጎረቤት የማይተዋወቅበት የመኖር ዘይቤ እየተስተዋለባቸው የሚገኙ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ቀስ በቀስ በገቢና በአመለካከት ፍፁም የተለያዩ ማህበረሰቦችን ከመፍጠሩ በተጨማሪ ወንጀል እንዲበረክትና መልካም እሴቶቻችንን የሚያፈርሱ የአኗኗር ዘይቤ ያላቸው ልምዶች እንዲፈጠሩ ምክንያት እየሆነ ይገኛል፡፡

ይህ ሁኔታ በዋነኛነት በዘፈቀደ በሚደረግ ወይም ለጉዳዩ ተገቢው ትኩረት ሳይሰጥ በተደረገ የቦታ አሰጣጥ ሂደት የሚከሰት ነው፡፡ ስለሆነም የከተማው ፕላን ይህን ችግር በመቅረፍ ረገድ ቁልፍ ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ አሮጌ የከተማውን ክፍሎች ለማደስ ሂደትም ሆነ በማስፋፊያ አካባቢዎች ለሚደረጉ የልማት ዕንቅስቃሴዎች የሚዘጋጁ የአካባቢ ልማት ፕላኖች (Local Development

Plans) ሁሉንም አይነት የከተማ ነዋሪ ሊያስተናግዱ የሚችሉ፣ ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት የሰጡ እና ግለኝነትን ሳይሆን አብሮነትን የሚያበረታቱ መሆን አለባቸው፡፡

የአካባቢ ልማት ፕላኖች የመሬት አጠቃቀማቸው ሁሉን ዓይነት የኢኮኖሚ አቅም ያላቸውን ነዋሪዎች ሊያስተናግድ በሚችል መንገድ መነደፍ ይገባዋል፡፡ በዚህ ረገድ በሰፊው የተያዘው የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታዎችን ለዚሁ ዓላማ ማዋል ከመፍትሄ እርምጃዎች መሃከል እንደ አንዱ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የኮንደሚኒየም ቤቶች በአብዛኛው የመሃከለኛውንና የአነስተኛ ገቢ ያለውን የከተማ ነዋሪ እንደማሰተናገዳቸው ሁሉ በነባርና አዳዲስ በሚፈጠሩ አካባቢዎች ሆነ መመጣጠን በሌለባቸው የከተማው ክፍሎች ውስጥ እነሱን በማካተት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያቀፉ መንደሮችን በመፍጠሩ በኩል ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡

## 3. አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ ልማት ማካሄድ

የሚካሄዱት የልማት እንቅስቃሴዎች በተለይ የሚሰሩት መንገዶችና የሚገነቡት ሕንፃዎች በአብዛኛው አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ አይደለም፡፡ አዳዲስ መንገዶች ሲሰሩ ብዙውን ጊዜ የመንገዱ አካል የሆኑት የእግረኛ መንገዶች ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቁ አገልግሎት መስጠት ስለሚጀምሩ፣ አንዳንዶቹም መንገዶች የእግረኛ መንገድ የሌላቸው መሆኑ፣ የውሃ መፋሰሻዎች ክፍት ሰለሚተዉ፣ የእግረኛ መንገዶችና ሕንፃዎች ማየት ለተሳናቸውና በተሽከርካሪ ወንበር (wheel chair) ለሚጠቀሙ ታሳቢ ተደርገው ባለመሰራታቸው ምክንያት የአካል ጉዳተኛ ወገኖቻችን የአሳዛኝ አደጋዎች ሰለባ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴ (mobility) የተገደበ እንዲሆን ከማድረጉ በተጨማሪ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፏቸው ላይ ጫና እየተፈጠረባቸው ይገኛል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው እየተካሄዱ ያሉት የልማት እንቅስቃሴዎች በእርግጥም ሁሉን ዜጋ በእኩል ደረጃ እያስተናገዱ ስለመሆኑ ጥያቄ ማንሳት የሚያስፈልገው፡፡

የዚህ ችግር መንስኤ ሆነው ከሚጠቀሱት መሃል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡

- የመንገዶቹ እና የሕንፃዎቹ ፕላን ከመጀመሪያውኑ ሲዘጋጅ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ አለመሆኑ፤
- የግንባታ ፕላን አፅዳቂ የሆነው የመንግስት አካል የቀረቡለት የመንገድም ሆነ የሕንፃ ግንባታ ፕላኖች ለአካል ጉዳተኞችም ጭምር አመቺ መሆናቸውን ሳያረጋግጥ የግንባታ ፈቃድ መስጠቱ፤
- በግንባታ ወቅትም ሆነ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኃላ ገደላ ገደል የሆኑ ቦታዎች መተዋቸውና ተረፈ ግንባታ ሥራዎች በወቅቱ አለመነሳታቸው፤

- አንዳንድ የመሻሻል ምልክቶች ቢታዩም አሁንም በአካል ጉዳተኞች ላይ ህብረተሰቡና የመንግሥት አካላት ሊሰጥ የሚገባውን ያህል ትኩረት አለመስጠታቸው፤

ባጠቃላይ እነዚህና የመሳሰሉት ጉዳዮች እንደ ችግሩ መንስዔ ተደርገው ሊወሰዱና ከተማዋ ሁሉንም ነዋሪዎችዋን እኩል ማስተናገድ እስካለባት ድረስ አስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጣቸው ይገባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ አዳዲስ በሚሰሩ መንገዶችና ሕንፃዎች ላይ ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይከሰቱ ተገበውን ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

## 4. ለመኪና ማቆሚያ (car parking) በቂ ቦታ ማዘጋጀት

ከብዙ እኩያ የውጭ ሃገር ከተሞች አንፃር ስትታይ አዲስ አበባ በቁጥር ብዙ መኪና የሌላት ብትሆንም ባለው የኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት የነዋሪዎች ገቢ እያደገ መምጣቱን ተከትሎ ተሽከርካሪ የመግዛት ፍላጎቱ በመጨመሩ ምክንያት የከተማዋ መኪና ቁጥሮች በከፍተኛ መጠን እያደገ መሆኑ በግልፅ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ግን አሁን ላለው የተሽከርካሪ ቁጥር እንኳን የሚመጥን የመኪና ማቆሚያ ቦታ የለም፤ ጉዳዩም ተገቢው ትኩረት የተሰጠው አይመስልም፡፡ እስካሁን ባለው ሂደት በጣት ከሚቆጠሩት ውጭ መንገዶችና ሕንፃዎች ሲገነቡ አብዛኞዎቹ ለመኪና ማቆሚያ በቂ ቦታ አልያዙም ወይም ከነጭራሹ በዕቅዳቸው ውሰጥ አላካተቱም ማለት ይቻላል፡፡

ለዚህም ብዙ የከተማ ክፍሎችን መጥቀስ የሚቻል ሲሆን በተለይ አዲስ የተጠናቀቀውና የከተማዋን ውበት ከጨመሩት መንገዶች መሃል አንዱ የቦሌ መንገድ ነው፡፡ ይህ አካባቢ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት እንደመሆኑ ቁጥራቸው የበዛ የንግድ ተsማት የሚገኙበትና የተsማቱን አገልግሎት ፈልገው ብዙ ሰዎች የሚንቀሳቀሱበት አካባቢ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ የሆነ የመኪኖች እንቅስቃሴ ያለው በመሆኑ አዲሱ መንገድ ይህን ታሳቢ አድርጎ የመኪና መቆሚያ አካቶ መሰራት ሲገባው ከነጭራሹ መኪና ማቆም የማይቻልበት ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህም በአካባቢው ባህሪ ምክንያት ከተፈጠረው ከፍተኛ የሆነ የተሽከርካሪና የሰዎች ክምችት አኳያ ሲታይና ከከተማ ፕላን ሙያ አስተሳሰቦች አንፃር ሲመዘን አብሮ የማይሄድና መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በቦሌው መንገድና በሌሎችም አካባቢዎች ያለውን የመኪና ማቆሚያ ችግር ለመፍታት ባደጉ ከተሞች ውስጥ እንደሚሰራበት ዓይነት በግል ባለሃብቱ የሚሰሩና (ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትን አደራጅቶ በዚህ ሥራ ውስጥ ማሳተፍ እንደአማራጭ ሊታይ ይችላል) በክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ ባለፎቅ የመኪና ማቆሚያዎችን በየአካባቢው እንዲሰሩ ማበረታቻ በመስጠትም ጭምር እንዲሰሩ ማበራራት ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህ ተግባራዊ ቢሆን በእርግጥም ድርብ ጠቀሜታ

አለው፡፡ በአንድ በኩል የመኪና ማቆሚያ ችግሩን የሚያቃልል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ይሆናል፡፡

ወደፊት በከተማዋ ውስጥ የሚሰሩ መንገዶች ደግሞ በጥናት ላይ የተመሰረተ ሆኖ በየተወሰነ ርቀት የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን አካተው መሰራት ይገባቸዋል፡፡ በተለይ ከቀላል ባቡር ግንባታው ጋር ተያይዞ የባቡሩንና የከተማዋን የአውቶቡስና ታክሲ አገልግሎቶች ለማቀናጀት እንዲቻል (የአውቶቡስና የታክሲ አገልግሎቶች ሥምሪታቸውን ከቀላል ባቡሩ ስምሪት ጋር እንደሚያጣጥሙ ይጠበቃል) እንደአመቺነቱ በቀላል ባቡሩ ማቆሚያ ፌርማታዎች አካባቢ ወይም በቅርብ ርቀት ለአውቶቡስና ለታክሲ ማቆሚያ ቦታ ማደራጀት የግድ ይላል፡፡ ይህም ነዋሪዎች ከአንዱ የትራንስፖርት ዓይነት ወደ ሌላው በቀላሉ እንዲቀይሩ በማድረግ የከተማዋን የትራንስፖርት መረብ እርስ በእርሱ የሚመጋገብ፣ የተቀናጀና ለነዋሪዎችም የተመቸ ያደርገዋል፡፡

ከዚህ ሌላ ቀደም ሲል ከተገነቡት ሕንፃዎች መሃል ጥቂት የማይባሉት ለመኪና ማቆሚያ ተብሎ የተሰራውን ቦታ ለሌላ አገልግሎት እያዋሉት በመሆኑ የከተማው አስተዳደር ክትትል በማድረግ እርምጃ በመውሰድ እንዲያስተካክሉ ማድረግ ይገባዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም አይነት ድርድር ማድረግ አያስፈልግም፤ እርምጃው ቆራጥ መሆን አለበት፡፡

የከተማ አስተዳደሩ ከላይ የተመለከቱትንና ሌሎች መፍትሄ የሚያመጡ እርምጃዎች በመውሰድ ከተማዋ አሁን ያለባትንና ወደፊት ገዝፎ ሊመጣ ምልክት እያሳየ ያለውን የመኪና ብዛት ሊያስተናግድ የሚችል የመኪና ማቆሚያ አገልግሎት መስጫ ቦታዎችን ከባለሃብቶች ጋር በመሆን ማደራጀት ትኩረት ሰጥቶት ሊሰራበት ይገባል፡፡

## 5. የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን በጥራት መሥራት

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚካሄዱ የልማት ሥራዎች መሃል በህብረተሰቡ ተሳትፎ ጭምር የሚሰሩት በኮብልስቶን (cobblestone) የሚሰሩት የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ይገኙበታል፡፡ ይህ የኮብልስቶን ሥራ በየክልል ዋና ከተሞች የተሰራውን ያህል ጥራት እንኳን ባይኖረውም በአንዳንድ የከተማዋ አካባቢዎች ደረጃውን ጠብቆ ተሰርቷል ቢባልም ትንሽ በማይባል የከተማው ክፍሎች የተሰራው የኮብልስቶን ሥራ ግን ባለቤት የሌለው ይመስል በጣም የተበላሸና በግዴለሽነት የተሰራ በመሆኑ እየተበላሸ ይገኛል፡፡ መስኩም በሙስናና በኪራይ ሰብሳቢነት መታማት ጀምሯል፡፡

መንግሥት ይህን መስክ ሲጀምር ዋና መነሻው ሃሳብ ሰፊ የሥራ መስክ በመፍጠር የከተማዋን የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ጥራት ለማሻሻል መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው በማህበር ስም የተደራጁት ሳይሰሩ ሌሎችን በአነስተኛ ዋጋ በመቅጠር ከፍተኛ ገንዘብ በማጋበስ በኪራይ ሰብሳቢነት የተተበተቡ መሆኑንና ለሥራው ጥራት ምንም የኃላፊነት ስሜት

የሌላቸው መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ሆኖአል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ ተገቢው ፍተሻ ተደርጎ ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

የኮብልስቶን መንገድ ሥራ መሰረት ሳይኖረው በፍፁም መሰራት የለበትም፡፡ በዚህ ረገድ አዲስ አበባ እንደ ባሕርዳር ካሉ ከተሞች መማር ይገባታል፡፡ በዚያ የተሰሩትና በመሰራት ላይ ያሉት መንገዶች ጥራት ሚስጢር ሌላ ሳይሆን ጥሩ የመሰረት ሥራ (earth work) የተሰራላቸው፣ የሚጠቀሙበት የድንጋይ ዓይነት ጠንካራና በቀላሉ የሚፈረካከስ ባለመሆኑ፣ በኃላፊነት መንፈስ የሚሰራ በመሆኑና በስራውም ወቅት ተገቢው ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው ነው፡፡ አዲስ አበባም ከዚህ ተምራ ጥራትና ዘላቂነት ያለው የኮብልስቶን የውስጥ ለውስጥ መንገዶች መሥራት ይጠበቅባታል፡፡ እዚህ ላይ የግንዛቤ ችግርም እንዳለ ልብ ይሏል፡፡ የኮብልስቶን መንገድ ጥራቱን ጠብቆ በደንብ ከተሰራ ከአስፋልት መንገድ የበለጡ ብዙ ጥቅሞች ያሉት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ከአስፋልት መንገድ ሲነፃፀር የኮብልስቶን መንገድ ጥቅሞቹ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- ከዋጋ አንፃር ሲታይ ኮብልስቶን ከአስፋልት መንገድ ከሦስት እሰከ አራት እጅ ያነሰ ነው፣
- ከፍተኛ የስራ ዕድል ይፈጥራል፣
- የውጭ ምንዛሪ የማያስወጣና በአካባቢ ውስጥ ባለ ግብዓት የሚሰራ ነው፣
- ለጥገና በጣም ቀላልና ድንጋዩን መልሶ መጠቀም የሚቻል ነው፣
- ውሃ በቀላሉ ወደ መሬት እንዲሰርግ ያደርጋል፣
- ከአስፋልት መንገድ ይልቅ ብዙ ዕድሜ አለው (የቆዩ የአውሮፓ ከተሞችን ማየት ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ነው)፣
- በሥራው የሚሳተፉ ሰዎችን በቀላል ወጪና አጭር ጊዜ ሥልጠና ብቁ ባለሙያ ማድረግ ይቻላል፣
- ከአካባቢ ጥበቃ አንፃርም ሲታይ ከአስፓልት መንገድ በእጅጉ ይሻላል፣
- በጥራትና በሙያ ታግዞ ከተሰራ ውበት ያለውና የተለያዩ የአርት ሥራዎችን መስራት ያስችላል፣

## 6. የመንገዶችን ስያሜና የትራፊክ ምልክቶች መትከል

አዲስ አበባ በከፍተኛ ፍጥነት እየዘመነች በመምጣት ላይ ያለች ከተማ መሆንዋ የማይካድ ቢሆንም ዘመናዊነቱን ሙሉዕ ለማድረግ ከሚሰሩት ሥራዎች መሃል አንዱ መሆን የሚገባው ሙያዊ በሆነ አሰራር መንገዶችን መሰየምና የተሰጠውን ስም ደግሞ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ በየመንገዶቹ ላይ መትከል ይገባል፡፡ አንዳንድ የከተማዋ መንገዶች ስያሜ የተሰጣቸው ቢሆንም አይደለም ከውጭ ለመጣ በከተማዋ ነዋሪዎች የሚታወቁ አይደሉም፡፡ ይህም የሆነው ስያሜአቸውን የሚያመለክት

ምልክት የለም አሊያም የተቀመጡ ምልክቶች እንኳን ቢኖሩ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ያልተሰሩና መቀመጥ ባለባቸው ቦታዎች ያልተቀመጡ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ነዋሪው እንዳያያቸው ወይም ልብ እንዳይላቸው ሆነዋል፡፡

ልላው በከተማዋ ውስጥ የሚታው ችግር የትራፊክ ምልክቶች በአግባቡና መኖር በሚገባቸው ቦታዎች አለመኖር ነው፡፡ በተለይ አዳዲስ መንገዶች ተገቢው የትራፊክ ምልክት ለአገልግሎት ሲከፈቱ በአግባቡ የተደረገላቸው ባለመሆኑ ለትራፊክ ችግሮች መከሰት የተጋለጡ ሆነው ይገኛል፡፡ የትራፊክ ምልክት በተደረገላቸውም አካባቢዎችም ቢሆን ምልክቶቹ ወልቀው መቆሚያቸው ብቻ የቀሩባቸው ወይም ተጣመው ወይም በአግባቡ ባለመቀመጣቸው ለተገልጋዩ የማይታዩ ምልክቶች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም፡፡

ስለዚህ ስያሜ ላላቸው መንገዶች ምልክት ማድረግ፣ ስያሜ ለሌላቸው መንገዶች ደግሞ ስያሜ በመስጠት ምልክት ማድረግ የከተማዋን ዘመናዊነት ከማረጋገጥ ባለፈ አድራሻዎችን በቀላሉ ለማወቅ ስለሚያስችሉ በቶሎ ሊሰሩ የሚገባቸው ሥራዎች ናቸው፡፡

የትራፊክ ምልክቶችንም በተመለከተ በአግባቡና በተጠና መንገድ በሁሉም መንገዶች ላይ ማስቀመጥና ጉዳት የደረሰባቸውንም እየተከታተሉ ማደስ ተገቢ ይሆናል፡፡ ይህም ጤናማና የተሳለጠ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንዲኖር የራሱን ዕገዛ ያደርጋል፡፡

<u>**ማጠቃለያ**</u>

ከዚህ በላይ የቀረበው አስተያየት የአንድ ባለሙያ ግላዊ አስተያየት ሲሆን እንደማንኛውም ቅን ሀገር ወዳድ ዜጋ የአዲስ አበባን የልማት እንቅስቃሴ አካባቢን የጠበቀና ለሁሉም ነዋሪ ፍትሃዊ ሆኖ ለማየት ከመመኘት አንፃር የቀረበ መሆኑን እየገለፅኩ ሌሎችም ለሙያው ቅርበት ያላቸው ግለሰቦችና አካላት የተሻለች አዲስ አበባን ከመፍጠር አኳያ በዚህ ፅሁፍ ከቀረበው ሃሳብ ተነስተው ወይም የራሳቸውን አስተያየት በመስጠት የበኩላቸውን ቀና ምላሽ ቢሰጡ የተሻለ ወጤት ማየት እንደሚቻል አምናለሁ፡፡ ባደጉ ሃገሮች በከተሞቹ ዕድገት ጉዳይ ላይ የባለሙያዎች የሃሳብ ፍጭት የተለመደና ይልቁንም የየከተሞቹ አስተዳደሮች የሚያበረታቱትና ለውሳኔ የሚረዳቸውን ሃሳብ የሚወስዱበት መድረክም ጭምር ነው፡፡

በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ዕምነት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ራሱን ክፍት በማድረግና የሚቀርቡትን አስተያየቶች በቅን ልቦና በማየት ከመካከላቸውም ጠቃሚ የሚላቸውን በመውሰድ

ትክክል አይደሉም ብሎ ለወሰዳቸው ደግሞ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት በኃላፊነት መንፈስ መሥራት ይገባዋል ብዬ አምናለሁ፡፡

የሁላችን ተሳትፎ ካለ የምንመኛትን ያደገች ኢትዮጵያ እና የዘመነች አዲስ አበባ በሕይወት ዘመናችን ውስጥ ከማየት የሚያግደን ምንም ኃይል ሊኖር አይችልም፡፡

<u>**ማስታወሻ፡**</u>

*የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ የከተማ ፕላንና የከተማ ማኔጅመንት ባለሙያና በአንድ አውሮፓዊ ዓለም አቀፍ አማካሪ ድርጅት ውስጥ በፕሮጀክት አስተባባሪነት* (project coordinator) *እና በከፍተኛ አማካሪነት* (senior consultant) *ሆና በማገልገል ላይ የምትገኝ ባለሙያ ነች፡፡*